የሰበር መ/ቁ.18581

ህዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሥሐ ወርቅነህ

ወ/ሮ ስንዱ ዓለሙ

ወ/ሮ ሆሚዕና ነጋሽ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አመልካች፡- በአ/አ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጣቢያ ጠበቃ መሐመድ ሲራጅ

ተጠሪ፡- ሲ/ር ቀቡላ ከድር ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 30985 ጥር 24 ቀን 1997 ዓ.ም ተጠሪ የሶስት ወር ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ ትመለስ ሲል በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተሰርቷል በማለት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው በአመልካች ድርጅት በነርስነት በማገልገል ላይ እያለሁ መልቀቂያ አላመጣሽም በሚል ያለአንዳች ጥፋትና ማስጠንቀቂያ የሥራ ውሌን ስላቋረጠ ደመወዜ ተከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ፣ የማልመለስ ከሆነ በአንቀጽ 42(4)(ሀ)፣ በ39፣ በ38 እና በ35(1) መሠረት ሙሉ ካሣ የስንብት ክፍያ ክፍያው ለዘገየበት የ1 ወር የማስጠንቀቂያ ሁለት ወር ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ነው፡፡

የአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት ቀርቦ የበኩሉን ክርክር አድርጓል፡፡ በመልሱም ተጠሪዋን ያሰናበተው መልቀቂያ ልታመጣ ባለመቻሏ እንመልቀቂያ የሌላቸውን ባለሙያዎች እንዳይቀጠሩ ደግሞ የክልሉ ጤና ቢሮ መመሪያ እንዳወጣ፣ መልቀቂያ እንድታሚላ ማስጠንቀቂያ እንደሰጣት፣ የተጠሪ ሥራ ላይ መቆየት ደግሞ የጤና ጣቢያ የሙያ ፈቃድ ሊያስነጥቅና ድርጅቱንም ሊያዘጋ በሚችል ደረጃ ላይ በመድረሱ ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 26(1) መሠረት ውሉ የሚቋረጥበት ሁኔታ በመፈጠሩ ስለሆነ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም መመሪያው በአዋጅ ቁጥር 42/85 በተደነገጉት የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ውስጥ ሊሸፈን የማይችል የሥራ ማሰናበቻ ምክንያት አይደለም፡፡ በአዋጁም ወደፊት ሚ/ር መ/ቤት በመመሪያ የሥራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ሊደነግግ ይችላል አልተባለም፡፡ መመሪያው ከአዋጁ ያነሰ ሲሆን ከአዋጁ ይጋጫል፡፡ ከአዋጁ ሣይጋጭ ሊተገበር የሚችለው መልቀቂያ ያላገኘ ሠራተኛ መልቀቂያውን እንዲያገኝና እንዲሠራ አሠሪው ትጋትና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጎ መልቀቂያ ያላቸውን እንዲቀጥር ለማሳሰብ እንጂ የተቀጠሩትን ማሰናበቻ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ብሎ እስከ ስድስት ወር የሚደርስ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏት ወደ ሥራ እንድትመለስ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ወደ ሥራ መመለሱን ጥያቄ በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በማጽናት የወሰነ ሲሆን ደመወዙን ግን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በማሻሻል የ3 ወር ደሞዝ እንዲከፈላት ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች የሕግ ስህተት ተሰርቷል ሲል የካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም በመፃፍ ባቀረበው ማመልከቻ የሚያቀርባቸው ክርክሮች፤

- ተጠሪ የሥራ መልቀቂያ ማስረጃ ሣይኖራቸው በጤና ጣቢያችን መሥራታቸው በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመሪያ ተደነገገውን ክልከላ የሚቃረን በመሆኑ በድርጅታችን ላይ የተደቀነውን የመዘጋት አደጋ ለመከላከል፣የሥራ ውላችንን ለማቋረጥ መሠረት ያደረግነውን ከአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 26(1) የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግለጽ ባልሆነ ምክንያት በዝምታ በማለፍ፣ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ደግሞ በዝምታ መታለፉን ካለማረሙም በላይ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን መመሪያ የክልከላ ሕግ ድፍን ባለ ሁኔታ ተጠሪን አይመለከትም በማለት መመሪያውን በመጣስ ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት ስለሆነ፣ ሰበር ሰሚው ችሎት፣

- አንቀጽ 26(1) በዝምታ መታለፍ የሌለበት መሆኑን፣
- የክልከላው ድንጋጌ ከአዋጅ 42/85 ጋር የማይቃረን መሆኑንና መጣስ ሌለበት መሆኑን፣ በሰበር አርሞልን የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ እንዲሽርልን
  - በአዋጅ ቁጥር 42/85 ስለ ውዝፍ ደመወዝ የተወሰነ ነገር የለም እንጂ ቢኖር ኖሮ ትክክለኛ ቦታው በሕገወጥ መንገድ ውሉ ስለተቋረጠበት ሠራተኛ ልዩ ልዩ ክፍያዎች የተደነገገበት አንቀጽ 43 ሆኖ ሳለ ስለመደበኛ ደመወዝ አከፋፈል የሚደነግገውን ከውዝፍ ደመወዝ ጋር ግንኙነት የሌለውን አንቀጽ (54)ን በመጥቀስ የሥር ፍ/ቤቶች ያስተላለፉት የውዝፍ ደመወዝ ውሣኔ የሕግ ትርጉም ስህተት ስላለበት ስህተቱ ታርሞ ውሣኔውን ውድቅ እንዲያደርግልን።

  የሚሉ ናቸው።

አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ታዞ ተጠሪዋ መልስ እንድትሰጥ በታዘዘው መሠረት ሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርባለች። ዋና ዋና ክርክሮቹም፣

- መመሪያው በይግባኝ ባይ ላይ ግዴታ የሚጥለው መልቀቂያ የሌለው የጤና ባለሙያ እንዳይቀጠር ነው። ይግባኝ ባይ መመሪያውን በመጣስ ከተጠሪ ጋር የቋሚነት የሥራ ውል ከመሠረተ በኋላ ግን የሚገዛው በመመሪያ ሣይሆን በአሠሪና ሠራተኛ በአዋጅ ቁጥር 42/85 ነው። አዋጁ የሚቃረን ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች አዋጁን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ እንደማይሆን በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 192(2) ስር ተደንግገዋል።

- ይግባኝ ባይ የአዋጁን አንቀጽ 26(1) መሠረት አድርጎ ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱን ጠቅሶ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች ይህንን ክርክርን በዝምታ እንዳለፉት በመጥቀስ ተከራክሯል። ይህ አንቀጽ በውስጡ የሥራ ውል ከሠራተኛው በሆነ ምክንያቶች ወይንም ከድርጅቱ ድርጅታዊ አቋም ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ባላቸው ምክንያቶች የሥራ ውል ሊቋረጥ እንደሚችል ይደነግጋል። ይሁንና እነዚህ ሁኔታዎች ምን ማለት እንደሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 27 እና 28 በግልጽ ተደንግገዋል። በዚሁ መሠረት በአንቀጽ 26(1) ከድርጅቱ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሥራ ውል መሠረት



ካሣ ተከፍሎ የማሠናበቱ አማራጭ የሚወሰደው ከሥራ ግንኙነቱ ጠባይ የተነሣ የሥራ ግንኙነታቸው ቢቀነስ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል ሲሆን ነው። አመልካች የጤና ጥበቃ ሚ/ር መመሪያን ባለማክበር መልቀቂያ የሌላት ባለሙያ በመቅጠሩ ከክልሉ ጤና ቢሮ እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚችል ተነግሮታል። እርምጃውም ፍቃዱን ሰርዞ ክሊኒኩን እስከማዘጋት ሊደርስ እንደሚችል ተገልጾለታል። ይህም የተጠሪ የሥራ ውል ቢቀጥል ለድርጅቱ ህልውና አስጊ ሊሆን እንደሚችል ያመላክታል። በሌላም በኩል ለድርጅቱ መዘጋት ምክንያት ልትሆን ትችላለች ከሚላት ተጠሪ ጋር የሥራ ውል እንዲቀጥል ቢደረግ ግንኙነታቸው ጤናማ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ሕጉ የሰጠውን አማራጭ በመከተል የሥራ ውሉ ተቋርጦ ካሣ ተከፍሏት እንድትሰናበት ማድረጉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

የስንብት ክፍያን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 39(1) የሙከራ ጊዜውን የጨረሰና በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ከአሠሪው የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል። እንዲሁም የሥራ ውሉ ከሕግ ወጪ ተቋርጦ ሆኖም ለአዋጁ ቁጥር 43/1/2/3/ መሠረት ወደ ሥራው የማይመለስ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ እንደሚገባው በአዋጁ ቁጥር 43(4) ላይ ተመልክቷል። አመልካቹም የሥራ ስንብት ክፍያ መክፈል የለብኝም የሚል ክርክር የለውም። በመሆኑም ተጠሪ ከላይ በተገለፀው ሕግ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ ልታገኝ ይገባል።

የማስጠንቀቂያ ክፍያን በተመለከተ የአዋጁ ቁጥር 43/4/ሀ/ እና 44 ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ አሠሪው በአንቀጽ 35 ስለማስጠንቀቂያ የተጠቀሱት ሳያሟላ ሠራተኛውን ከሥራ ካስወጣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፍል እንደሚገባ ያስገነዝባል። በዚህ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጣት ለመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተመልክቷል። ተጠሪዋ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠኝም ስትል ያቀረበችውም ማስተባበያ የለም። በመሆኑም አመልካች በሕግ የተጣለበትን ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታውን የተወጣ ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ሊከፍል አይገባም።

የማዘግየት ክፍያ ጥያቄ ስንመለከት የሥራ ውል ሲቋረጥ የሠራተኛው ደመወዝ ከደመወዙ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሁሉ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል እንዳለባቸው የአዋጁ ቁጥር 36 ይደነግጋል፡፡ ሠራተኛው ከአሠሪው የተረከበውን ንብረት የማስረከብ ወይም የሚፈለግበትን ማናቸውም ሂሣብ በማወራረድ የራሱ ጥፋት በሆነ ምክንያት ካዘገየ ግን ክፍያው ሊራዘም እንደሚችል ይኸው አንቀጽ ይናገራል፡፡ በቁጥር 36 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለሠራተኛው መከፈል የሚገባውን ሂሣብ ያልከፈለ አሠሪ ክፍያው ለዘገየበት ጊዜ ለሠራተኛው ደመወዝ እንደሚከፍለው በቁጥር 38 ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ይገባታል የሚለውን ክፍያ ለመክፈል ዝግጁ እንደነበር ተጠሪ ግን ተጨማሪ ክፍያ በመፈለግ ክፍያውን ለመቀበል ፍቃደኛ እንዳልሆነች በስር ክርክሩ ገልጿል፡፡ ይህ ክርክር በተጠሪ በኩል የተስተባበለ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት አልተዘገበም፡፡ በሌላም በኩል የተጠሪ ዋና ክርክር ወደ ሥራ መመለስ ነው፡፡ የልዩ ልዩ ክፍያዎች አማራጭ በ2ኛ ደረጃ የቀረበ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ተጠሪ ክፍያው ተቀብሎ ለመሰናበት ፍቃደኛ እንዳልነበረች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በነዚህ ምክንያቶች ክፍያው የዘገየው በአሠሪው ጥፋት ነው ለማለት ስለማይቻል አመልካች የመዘግየት ክፍያ መክፈል የለበትም፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ላልተሠራበት ጊዜ ደሞዝ ሊከፈል እንደማይገባ የሰበር ችሎት በመዝ/ቁጥር 17/89 አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን አንቀጾች የተረጎመ ስለሆነ ተጠሪ ያቀረበችው የውዝፍ ደሞዝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጡት ውሣኔ ይህም ችሎት ተስማምቶበታል፡፡
2. የተጠሪ ወደ ሥራ መመለስ በአመልካቹ ህልውና ላይ ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ይህም የግራ ቀኙን ግንኙነት ጤናማ ስለማያደርገው ተጠሪዋ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 43(3) መሠረት ካሣ ተከፍሏት እንድትሰናበት ተወስኗል፡፡ እንዲሁም የስንብት ክፍያ እንዲከፈላት ተወስኗል:
3. የካሣውን መጠን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 43(4)(ሀ) መሠረት ተሰልቶ እንዲከፈላት ተወስኗል፡፡ የሥራ ስንብት ክፍያም በአዋጁ ቁጥር 40/1/እና /2/ መሠረት ተሠልቶ እንዲከፈላት ተወስኗል፡፡
4. የፌዴራል መጀመሪያና የከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 5984 እና 30985 ተጠሪዋ ወደ ሥራ እንድትመለስ የሰጡት ውሣኔ ወደ ሥራ መመለሷ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ባለማገናዘብ በመሆኑ ውሣኔዎቹን



በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር.348(1) መሠረት በድምጽ ብልጫ ተሽሯል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡ የውሣኔዎቹን ግልባጭ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የሐሣብ ልዩነት</u>

እኔ ስሜ በሁለተኛ ተራ የተመለከተው ዳኛ ከላይ በተመለከተው በአብዛኛው ድምጽ ፍርድ ስለአልተስማማሁ የሚከተለውን የሐሣብ ልዩነት አስፍሬያለሁ፡፡

ሠራተኛዋ ከአሰሪዋ ጋር ባላት የሥራ ግንኙነት የተፈጠረ ችግር አለ አልተባለም፤ ችግር አለ የተባለው አሰሪዋ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር ባለው ግንኙነት ነው፤ ችግሩም አሰሪው ሠራተኛዋን ካላሰናበተ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እርምጃ ይወስድባታል የሚል ነው፤ እንደተባለው ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአሰሪው ላይ እርምጃ ሊወስድበት እርምጃውን በሕጉ መሠረት መከላከል እንጂ፣ ሚኒስቴሩ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል ተብሎ፣ የአዋጅ አንቀጽ 43/3/ ከሚለው ውጭ ሠራተኛዋ ወደ ሥራዋ እንዳትመለስ በመወሰኑ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡